# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

☏ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251 116– 55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia e-mail:-allethiopiaunityparty@gmail.com

# ALL ETHIOPIA UNITY PARTY


ቁጥር
Ref No. __________________
ቀን
Date____________________

ለሰሜን አሜሪካ፣ ለካናዳ፣ ለአውሮፓ፣ ለአውስትራሊያ እና ለደቡብ አፍሪካ
የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች
<u>በያላችሁበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>ከአመራርነትና ከአባልነት የታገዱ ግለሰቦችን ስለማሳወቅ</u>

ገዥው ፓርቲ የኢትዮጵያ ህዝብ አለኝታ የሆነውን አንጋፋውን ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ መኢአድን ለማፍረስ ከክቡር ፕሮፌሰር ዓሥራት ወልደየስ ጀምሮ በየደረጃው የነበሩ አመራሮችን እና አባላትን ገድሏል፤ አሳድዷል፤ ሰውሯል፤ አካላቸውን አጉድሏል፤ ንብረታቸውን ወስዷል፤ መሬታቸውን ነጥቋል፤ በሀሰት በመወንጀል በገንዘብ እና በእሥራት ቀጥቷል፤ ከሥራ አፈናቅሏል፡፡ በህወሃት ፍፁም የበላይነት የሚመራው የገዥው ፓርቲ ሁሉንም ህገ-ወጥ መንገዶች በመጠቀም መኢአድን ለማጥፋት ተደጋጋሚ ሙከራ ቢያደርግም አልሳካ ስላለው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ስልቱን ቀይሮ ሌሎች ችግሮች እየፈጠረብን ይገኛል፡፡ ይኸውም፣ በውስጣችን የተሰገሰጉ ሰርጎ ገብ ባንዳዎችን እና ስብዕናቸውን በገንዘብ የሸጡ ማስተዋል የጐደላቸው ግለሰቦችን በመጠቀም አንጃ በመፍጠር አባላትን እና አመራሩን በመከፋፈል ሙሉ አቅሙን በመጠቀም ከፍተኛ ደባ በመፈጸም ላይ ነው፡፡

ፓርቲያችንን ሰው አልባ ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ እና ሲቦረቡሩ የነበሩትን የእነ አቶ ማሙሸት አማረ ቡድንን በመደገፍ በህግ ሳይሆን በመመሪያ የሚሰራ የዳኝነት ተቋሙን በመጠቀም የፓርቲያችንን ዋና ጽ/ቤት ሀምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም በታጠቀ ኃይል አስከብቦ በሩን በሀይል በመክፈት በአቶ ማሙሸት አማረ ለሚመራው አንጃ የማስረከብ እርምጃ መውሰዱ ይታወሳል፡፡ ነገር ግን አዲስ አበባ የሚገኙ አባላት እና አመራሮች አካላቸው በአሲድ ሳይቀር ተቃጥሎ እና ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለው የወያኔ እና የተላላኪዎቹ እቅድ መክሸፉ ሁላችሁም የምታውቁት ሃቅ ነው፡፡

በቅርቡ ደግሞ በአቶ ማህተመ በኩረ የሚመራ ጥቂት አባላት ያሉት አዲስ አፍራሽ ቡድን የተፈጠረ ሲሆን ይህ ህገ ወጥ አካል እንደእነ አቶ ማሙሸት አማረ ሁሉ የፓርቲውን ማህተም በግሉ ይዞ ለ2 ወር ያህል የድርጅቱ ሥራ እንዳይሰራ በማድረግ ትግሉን ለማንኮላሸት ተንቀሳቅሷል፡፡

የአፍራሽ ቡድኑ አባላት÷

1. አንጃ ፈጥረው በህገ ወጥ መንገድ ተንቀሳቅሰዋል፡፡
2. ጠቅላላ ጉባዔው እና ማዕከላዊ ምክር ቤቱ የጣለባቸውን ኃላፊነት በመዘንጋት ከአምስት ሳምንት በላይ ምንም ዓይነት ሥራ ካለመሥራታቸው በተጨማሪ

ከአምስት ጊዜ በላይ በመደበኛው የስብሰባ ቀን ባለመገኘታቸው በስልክ እና ሁለት ጊዜ ደግሞ በደብዳቤ ጥሪ አድርገንላቸው ለመምጣት ፈቃድኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡

3. የፓርቲውን ፕሬዝዳንት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን በሐሰት በመወንጀል በአድማ እና በህገ-ወጥ መንገድ ከኃላፊነት ለማንሳት እና ፓርቲውን በመሸጥ ተለጣፊ ድርጅት ለማድረግ ጥረት አድርገዋል፡፡

4. የፓርቱውን ዋና ፀሀፊ አቶ ተስፋዬ ታሪኩን በሌላቸው ሥልጣን አግደናል ብለው መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

5. የፓርቲውን ማህተም በመያዝ ለሁለት ወር ያህል ሥራው እንዲቋረጥ እና ትግሉ እንዲንኮላሽ ከፍተኛ ደባ ፈጽመዋል፡፡

6. የግል ጥቅማቸውን ለማሟላት ፓርቲውን እና አባላቱን መነገጃ ለማድረግ በህገ-ወጥ መንገድ በድብቅ በመኢአድ ስም ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ካቴድራል ቅርንጫፍ የሂሳብ ቁጥር 4393 የባንክ ሂሳብ ከፍተዋል፡፡

7. በ30/11/03 ዓ.ም ማዕከላዊ ም/ቤቱ ያሳለፈውን ውሳኔ እና ያፀደቀውን የሥራ ክፍፍል አንቀበልም ብለዋል፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም ፀረ-መኢአድ እንቅስቃሴዎች አድርገዋል፡፡

በእኛ በኩል በመኢአድ ላይ አፍራሽ ተልዕኮ እየተወጡ ያሉት ግለሰቦች ከተሳሳተውና ነገ በታሪክ እና በትውልድ ፊት ከሚያስጠይቃቸው እኩይ ተግባር ተላቀው ወደ ፓርቲው እንዲመለሱ፣ የድርጅቱንም ማህተም እንዲያስረክቡ እንዲሁም የፓርቲያችንን ሥራዎች ባግባቡ እንዲከናወኑ ሆደ ሰፊ ሆነን በተደጋጋሚ በስልክ እና በደብዳቤ ጥሪ አቅርበን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ ምንም እንኳ ነፃ ምርጫ ቦርድ እና ነፃ የዳኝነት ተቋም እንደሌለ ብናውቅም አማራጭ ስለሌለን ለሁለቱም አካላት አመልክተን ሌላ አዲስ ማህተም አስቀርፀን ሥራውን ጀምረናል፡፡

ግለሰቦቹ መኢአድን ለማዳከም በአገር ውስጥና በውጭም እየፈጸሙ ያሉት እኩይ ተግባሮች እየጨመሩ በመምጣታቸው ይህን ለማስቆም እንዲሁም እኛም የተነሳንለትን ዓላማ የበለጠ ለማከናወን እና ትግሉንም አፋፍሞ ለመቀጠል አሁንም በድጋሚ ውስጣችንን ማፅዳት ተገቢ እርምጃ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሰባት ድረስ የተዘረዘሩት የአንጃው ቡድን ጥፋቶች በፓርቲያችን መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ

- 22.5.10. ጎሰኝነትና ማንኛውም ዓይነት ጽንፈኝነት፣
- 22.5.11. የፓርቲውን ኅብረት ሊያናጋ በሚችል በአንጃኝነት መቧደን፣
- 22.5.12. ከተመደቡበት የሥራ አስፈጻሚ አባልነት ወይም ሌላ ኃላፊነት በተከታታይ ካለፈቃድ ከሦስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ መቅረት ወይም ሥራ ላይ አለመገኘት እና
- 22.5.13. የጠቅላላ ጉባዔ ወይም የማዕከላዊ ምክር ቤት ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔና ትዕዛዝ አለመፈጸም፣

በሚሉት ውስጥ የሚካተቱ ሲሆኑ በአንቀጽ 22.5. ከአባልነት የሚያስወግዱ ተግባራት ናቸው፡፡

የመኢአድ ማዕከላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በ18/02/2004 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ የአፍራሹ ቡድን አባላት የፈጸሟቸውን ጥፋቶች መርምሯል፡፡ በመሆኑም የፓርቲውን ህልውና ለማስጠበቅ በሙሉ ድምጽ ባሳለፈው ውሳኔ እና የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 20.1.11. ለፕሬዝዳንቱ በሰጠው ኃላፊነት መሠረት ከዚህ የሚከተሉት ግለሰቦች ከአመራርነትም ሆነ ከአባልነት እንዲታገዱ ተስማምቷል፡፡

እነሱም÷

1. አቶ ፀጋዬ ግዛው - የህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ኃላፊ የነበሩ፣
2. ዶ/ር በዛብህ ደምሴ - የውጭ ጉዳይ ኃላፊ የነበሩ፣
3. አቶ አቤል ሙሴ - የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ የነበሩ፣
4. አቶ ብርሃኑ ወ/ሰንበት - የምዕራብ ቀጠና ኃላፊ የነበሩ፣
5. ሻምበል ግዛው ተሰማ - የምስራቅ ቀጠና ኃላፊ የነበሩ፣
6. አቶ በለጠ ገብሬ - የሰሜን ቀጠና ኃላፊ የነበሩ እና
7. ወ/ሮ ዕፀገነት ይልማ የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ የነበሩ፣ ከአመራርነትም ሆነ ከአባልነት እንዲታገዱ እና ጉዳያቸው ለህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ እንዲቀርብ ወስኗል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም÷

1. አቶ ማህተመ በኩረ - የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ የነበሩ፣ የፓርቲውን ማህተም ለአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊው አላስረክብም በማለታቸው፣ አሉቧልታ በመንዛት አባላትን በመከፋፈላቸው፣ የፓርቲውን ገንዘብ በማባከናቸው እና አፍራሹን ቡድን በማስተባበር ተግባር ላይ በመገኘታቸው ከመስከረም 15 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ታግደው ጉዳያቸው በሚመለከተው አካል በመታዬት ላይ ይገኛል፡፡

2. አቶ አሡፋ ሀብተ ወልድ - ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩ፣ ነሃሴ 17/2004 ዓ.ም በጻፉት ደብዳቤ ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ጠይቀው የነበረ ሲሆን ጉዳዩን ከመረመርን በኋላ በ18/01/2004 ዓ.ም የስንብት ደብዳቤ ተፅፎላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአንጃው ቡድን ውስጥ በማስተባበር እንቅስቃሴ ላይ የሚገኙ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ጥቅምት 16/2004 ዓ.ም ከመኢአድ አባልነት ታግደዋል፡፡

3. አቶ ጌታቸው ባያፈርስ - የትምህርት፣ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ ኃላፊ የነበሩ፣ መልቀቂያ በማቅረባቸው አመራሩ ሃሳባቸውን እንዲቀይሩ ጥያቄ አቅርቦላቸው ወደ መኢአድ መመለሳቸውን ገልጸው የተለያዩ ተሳትፎዎች ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡ ነገር ግን ሃሳባቸውን ሲቀይሩ መልቀቂያ በጽሁፍ እንዳቀረቡ ሁሉ መመለሳቸውንም በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ተገልጾላቸው ይህን ሳያደርጉ ቀርተዋል፡፡ መኢአድ ውስጥ እያሉ ነሐሴ 25 ቀን 2003 ዓ.ም ወደ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ጽ/ቤት በመሄድ 50.00 ብር የአባልነት መመዝገቢያ እና 20.00 ብር የነሃሴ ወር 2003 ዓ.ም ወርሃዊ ክፍያ ክፍለው በአንድ ጊዜ የሁለት ፓርቲዎች አባል በመሆን ህገ ወጥ ተግባር አከናውነው ተገኝተዋል፡፡ በዚህ ህገ ወጥ ተግባራቸው እንዲሁም የአፍራሹ ቡድን አባል ሆነው በመገኘታቸው ከአመራርና ከአባልነት ታግደዋል፡፡

በየደረጃው የምትገኙ አመራሮች፣ አባላት እና ደጋፊዎቻችንን እንዲሁም በመላው ዓለም የምትገኙ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች!
ከላይ ስማቸው የተዘረዘሩት ህገ ወጥ ግለሰቦች በመኢአድ ስም ማንኛውንም ዓይነት መግለጫ ከመስጠትም ሆነ ሌሎች እንቅስቅሴዎችን ከማድረግ እንዲቆጠቡ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑንም ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

መኢአድን ለመታደግ እንዲሁም ውስጣችንን ከሰርጐገቦች አፅድተን ወደ ወሳኙ ትግል ለመግባት ከሚያስፈልጉ ዋና ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ታዋቂ ምሁራንን ወደ አመራር ማምጣት መሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑ ባደረግነው ከፍተኛ ጥረት ከላይ የተገለፁትን ሰዎች የሚተኩ ታላላቅ እና ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸው የተወሰኑ ምሁራንን ያዘጋጀን መሆኑን በደስታ እንገልጻለን፡፡

ውድ የመኢአድ አባላት በሙሉ! በየፌርማታው እየተንጠባጠቡ ከሚቀሩ አስመሳዮች እራሳችሁን በመጠበቅ ዛሬም እንደትናንቱ ከጐናችን በመቆም ትግሉን አጠናክረን እንቀጥል ዘንድ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!

ኃይሉ ሻውል ግዛው (ኢ/ር)
የመኢአድ ፕሬዝዳንት
Hailu Shawel Gezaw
AEUP President (Eng)

ጥቅምት 19,2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ